
# መልስ “አጋዴን” እንጂ “ኢትዮጵያዊያን” አይደለንም ለሚሉ! (ከጌታቸው ረዳ) Ethiopian Semay ድረገጽ አዘጋጅ




ሰሞኑን የጤና መታወክ ቢይዘኝም፤ ምሁራኖቻችን የጠላት ፕሮፓጋንዳ በኢትዮጵያ ድረገፆች እየተለጠፈ እያነበቡ በቸልተኝነት የጠላት ፕሮፓጋንዳ በኢትዮጵያዊያን ድረገጾች ሲስተናገዱ ዝም ብለው ሲያልፏቸው ያመኛል። ይህ

ቻልተኝነታቸው የለመደባቸው ቢሆንም፤ የቻልተኛነት ተባባሪነታቸው ሲከነክነኝ ከነ ሕመሜ ለጠላቶች (ለንህሊስቶች) መልስ ለመስጠት ተገድጃለሁ። ለዚህ እናንት የኔ ተከታዮች ምንም ብትታመሙ፤ ምንም ብትደክሙ እስከመጨረሻ ድረስ ለጠላቶች ትንፋሽ መስጠት እንዳይለምዳችሁ በሚል ነው ይህ ጽሑፍ ዛሬ ለመጻፍ ያነሳሳኝ።

በኢትዮጵያዊአን እና በውጭ ሰዎች ሕሊና የግዝገዛ ዝርጋታቸውን (ዲስትሪቡሽን) ለመዘርጋት ቀላል ሆኖ ያገኙት ቀንደኛ ጠላቶችና ተገንጣዮች ሁሉ ሳይቀሩ የሚሽቀዳደመበት ቆሻሻ ጸረ ኢትዮጵያ ቅስቀሳቸውን የሚያፈሱበት ዘሓበሻ በተባለው ድረገጻ ላይ ነው። ሰሞኑን ባለተራ የሆነው “ኦብነግ” እያለ ራሱን የሚጠራ ሲያሻውም “ኦጋዴኖች እስላማዊ አረቦች ነን እያለ መሪያቸው የሚለፍፈው” ድርጅት “Ogaden-Ethiopia Peace Talk may Resume” (February 6, 2015) እና Ogaden-Ethiopia Peace Talk may Resume, (February 10, 2015) በሚል የኦጋዴን ነፃ አውጪ ነኝ ባይ ድርጅት ጸረ ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳ በዘሐበሻ ድረገጽ ሳምንት ባልሞላ ውስጥ ሁለት ጊዜ ተልጥፎ አንባባችሁ ይሆናል። ዋዜማ እያለ የኦሮሞ ጥያቄ እያለ የሚያደነቁረን ሌላው ራዲዮም እየተከታተላችሁ ነው። ይህም በዛው ድረገጽ በተከታታይ

እየተለጠፈለት ነው። ለሁሉም ትዝብት ነው።




ለምንድነው እንደዚህ የምለው? ምክንያት አለኝ። በድረገጾቻችንም ሆነ ጉጉል ላይ የድሮ ህጋዊ የአገራችን ካርታ ፍጹም አታገኙም። የምታገኙት ከ1981 ወዲህ የተፈጠረው አስቀያሚው የወያኔ፤ ኦብነግ/ኦነግ እና ሻዕቢያ ካርታዎችንና ቅርምቶች የተሞላ ነው። ለምን እንዲህ ሆነ? ምክንያቱም ምሁራን ኢትዮጵያዊያንና ድረገጾች የጠላቶችን ፕሮፓጋንዳ እየተጋሩ ስለሚለጥፉና ስለሚያስፋፉላቸው ነው። ፕሮፐጋንዳቸው ሲለጥፉ በአንባቢ ሕሊና የሚቀርጹት ነገር አለ። የት አንዳገኘሁት አላውቅም እንጂ በፋይሌ ያስቀመጥኩት የሚከተለውን እውነታ አንብቡልኝ ፡

“The media determines our language, our language shapes our

thoughts, and our thoughts determine our actions. Language is the fulcrum of a society's perception. Whosoever controls the public's language controls the public's perception" ይላል።

ለዚህም ነው ኢትዮጵያዊያን የጠላት ካርታዎች እና ፕሮፓጋንዳዎችን እያናፈሱ ወደ ሕዝብ በቀላሉ ከመዘርጋት ድረገፆች ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው እያልኩኝ የምነታረከው።

የኡብነት ዜና ከርዕሱ መነሻ ስትመለከቱት ድረገጹ "ኢትየጵያ እና ኦጋዴን" ድርድር ሊያደርጉ ነው የሚው እንዲለጠፍ ሲፈቅድ (ወይንም እራሱ አዘጋጁ ሁሌም እንደሚያደርገው ፈልጎ ከጠላቶች ድረገጽ ቀድቶ ለጥፎት ሊሆንም ይችላል) እንዲህ ያለ ሕግ ያላወቀው የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛትን የሚጻረር "አስነዋሪ ርዕስ" ለምን ተለጠፈ? የሚል ስሜት አሳድሮብኛል። መልሱ የሚገኘው ከድረገጹ አዘጋጅ ከወጣት ሔኖክ አለማዮህ ቢሆንም አንባቢዎች ግን የየራሳችን ግንዛቤ ስለሚኖረን- ኦጋዴን እና ኢትዮጵያ የሚባሉ ሁለት አገሮች አሉ ወይ ለሚለው ጥያቄ ድረገጾች አገርን በማፍረስ የፕሮፓጋንዳ ሳብቨርዥን "ግዝገዛ" ሴራ ላይ አውቀው ወይንም ሳያውቁ? የሚለውን ጥያቄ መለስ ለማግኘትም ቢሆን እሱን ላሁኑ ወደ ጎን ልተወው እና ወደ ተገንጣያች እና አፍራሽ ቅጥረኞች መልስ ለመስጠት ወደ ዘርዝር ሐተታዬ ይገቤአችሁ ልግባ።

(ይህ አጋጣሚ ተጠቅሜ ላመሰግን የምፈልገው "ኢትዮጵያኒዝም ቲ.ቪ" በሚል በዩ ቱብ ድረገጽ ላይ በፕሮፌሰር ሙሴ ተገኝ አዘጋጂነት የሚቀርብ የወጣት የተወያዮች ክብ የጠረፔዛ ውይይት እጅግ ቁም ነገር ያዘለ እና በተወያዮቹ እና ባዘጋጁ መሃል የሚደመጠው ያገራችን አንደበታዊ አስደሳች በአወያዩ እና በተወያዮቹ መሃል የሚከሰት ድንገተኛ ቤተሰባዊ ሳቅና ፈገግታ የሚያስከትል አዝናኝ ንትርክ እንዲሁም ቁም ነገር ያዘለው ፖለቲካዊ ውይይትና ልውውጥ ስለወደድኩላቸው ተወያዮቹ እና አዘጋጁ ላመሰግን እወዳለሁ። ኢትዮጵያዊነትና ኢትዮጵያነ ለማፍረስ ለማፍረስ በተቃዋሚው ጎራም ሆነ በወጣላቸው ጠላቶቻችን ግዝገዛው ሲጧጧፍ አገር ወዳዶችም ባገኙት መድረክ መከላከያ መስመራቸውን መቀጠል ተገቢ ነው። አሁን ወደ ዋናው ርዕሴ ልግባ።

የኦጋዴን ጋዜጠኛ ነኝ ባዩና በዘሓበሻ ድረገጽ የተለጠፈው "Ogaden-Ethiopia Peace Talk may Resume" (February 6, 2015) እና Ogaden-Ethiopia Peace Talk may Resume, (February 10, 2015) በመሚ ርዕስ የተዘረጋው የታሪክ ውሸት እንዲህ እንዲህ ይነበባል። Ogaden borders- "Djibouti, Oromia, Kenya and Somalia" The people are predominantly ethnic Somali and Muslim. "The region was Italian and English-colony but in 1954, the English handed over Ethiopia" - Ogadentoday - See more at: http://www.zehabesha.com/ogaden-ethiopia-peace-talk-may-resume-ogadentoday-says/#sthash.Y2e4g1GB.dpuf

እንዲህ ያለው ዓይን የሌለው ዕውር ውሸትና አገር አፍራሽ የፕሮፖጋንዳ ግዝገዛ ምሁራን እና ድረገፆች በቸልተኝነት ሲለቁት ያሳዝናል።

አጭሩ መልስ **"ኦጋዴን"** የሚባል አገር በታሪክ አይታወቅም። ኦጋዴን ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ አካል አንዱ ነው። ሁለተኛ አሮሚያ የሚባል አገር ከቶ በታሪክ ተሰምቶ አይታወቅም። ሁለቱም እንደ አገር የሚጠቀሱት በከሰሩ ማንነታቸው በተዋዝቀባቸው የሕሊና በሽተኞች የሚቃዥ ቅዠት ነው። አንዳንዶቹ የኦነግ መሪዎችም ክስረታቸውን እያዩት ሲመጡ ለተንኮል ሲሉ ዘዴአቸውን በመቀየር ላይ ናቸው። ያም ሆኖ ውሎ አድሮ ወድቀት ነው።

ዓረብ ነኝ የሚለው የኦጋዴኑ ደግሞ አስገራሚ ነው። ካሁን በፊት እንደገለጽኩላችሁ የኦጋዴን ነፃ አውጪ መሪ ነኝ የሚለን የሶማሌው ሲያድ ባሬን በባሕር ሃይል በወታደርነት ሲያገለግል የነበረው የዚህ ድርጅት ያሁኑ መሪ ነኝ ባዩ አድሚራል መሀመድ ዑመር ዑስማን "ኦጋዴኖች አረቦች ነን" ሲል Asharq Al-Awsat ለተባለ አውሮጳ በሚታተም የሶማሊ ሚዲያ በአንደበቱ የተናገረውን በድረገጼ ላይ ከቃለመ መጠይቁ (ብርሃኑ ነጋ በየ አሜሪካ ግዛቱ ከኦብነግ አባሎች ጋር ኢትዮጵያዊያንን ሲያጃጅል በነበረበት ጊዜ) በራሴው ኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ እና በዘሓበሻ ድረገጽም ላይ "The Deluded Elite of the Liberation fronts (Part 1) By Getachew Reda) May, 10, 2011 - **See**

**more at: http://www.zehabesha.com/the-deluded-elite-of-the-liberation-fronts/#sthash.kvhEglJS.dpuf**

በሚል ርዕስ (Source Somal Swiss Community/Somalida Switzerland "ONLF leader claims Ogaden are "Arab people" under Ethiopian occupation..http: Somaliswisstv.com interview with Asharq Al-swak- source Los Angeles Times). - See more at: http://www.zehabesha.com/the-deluded-elite-of-the-liberation-fronts/#sthash.kvhEglJS.dpuf

የተገኘ ከ4 አመት በፊት በማስረጃ አቅርቤላችሁ ነበር። በተያያዥም ከአልሸባብ የሽብር ድርጅትም ተጓዳኝ ግንኙነት አንዳለው እንዲህ ሲል ይገልጻል "If these groups (Shabab) are fighting against Ethiopia, then we have a common enemy." ስለዚህም የጋራ ጠላታችን ኢትዮጵያን አብረን እንወጋለን ይላል። ከዚህ ተነስተን በሰነድ እና ታሪክ ያልተደገፈ የሌላ አገርንትን ስሜታቸው እና ነፃ አውጪነትን ውድቅ የታሪክ ድጋፍና መሰረት የሌላው ጥያቄአቸውን እንመልከት። ኢሳያስ አፈወርቂ እና ተኽለአብ ወ/ማርያም ትግሬዎች ሆነው ትግሬነታቸውነ ክደው ጣሊያን የሰየመላቸውን "ኤርትራ" የሚባል አዲስ የማንነት ፍላጋ አንደገቡት ማለት ነው፤ ኦብነጐችም ኦጋዴን እንጂ ኢትዮጵያዊያን አይደለንም እያሉን ያሉት።

እስኪ ጉዳዩን ገልጠን እንየው። ኦጋዴን የሚባል አገር እንግሊዞች በ1954 (ፈረንጅ ዘመን አቆጣጠር) ለኢትዮጵያ የሰጡት ቦታ ነው ብሎ መዋሸቱ እናቱ ገና ትንናት የወለደቺው "ታሪክ ያላነበበ ታዳጊ ህጻን" ወይንም "ዓረቦች ነን" የሚለው ቅዠታቸው ለማሳካት የሚቃዡ በሽተኛ የሆኑ ግለሰቦች ካልሆነ ኦጋዴን ከ1954 ሳይሆን ጥንት ታሪክ ሲፈጠር ጀምሮ ኦጋዴን የኢትዮጵያ አንጡራ መሬት ነው።

በመረጃ እንከራከር!

እስላማዊ ዓረብ ነኝ እያለን ያለው የኦጋዴን ነፃ አውጪ የሚባል በዘመነ አክሱም ፤ በዘመን ይሳቅ፤..የት ነበር ? እነሱ ዓረቦች በነበሩበት ዘመን፤ እኛ ግን ኦጋዴን ውስጥ እንኖር ነበርን። ታሩክን እስኪ እንመልከት።

ወዳጄ ምሁሩ ምሁሩ ዶ/ር ዳኒኤል ክንዴ አጋዴንን አስመልክቶ እንዲህ ይላል። በዚህ ትችቴ ዶ/ዳኒኤልን እንደ ዋቢ ስጠቅስ ሰተረጉሞው ስሕተት ካለው የኔ መሆኑን አንባቢ አስቀድሜ አንዲገነዘብልኝ እጠይቃለሁ።

( **Let us begin with the problems of sourcing.)** – "As is usually done, the accuracy of the information gathered from external sources should be checked and counter-checked by consulting local sources, or the other way. To be able to do that, apart from professional training, one needs mastery of languages as well as of the relevant literature. While there have been outstanding foreigners who wrote about Ethiopian history in a professional manner, there have also been pseudo- intellectuals, who have attempted to re-write Ethiopian history, and whose writing has had no purpose except to advance the interests of those who financed their research. By simply relying on the information collected from the colonial archives, such "scholars" still profess to have written a history of Ethiopia without consulting Ethiopian sources. The Ethiopian viewpoint is not represented. After all, there are two sides to an issue."

"………. By simply relying on the information collected from the colonial archives, such "scholars" still profess to have written a history of Ethiopia without consulting Ethiopian sources. The Ethiopian viewpoint is not represented. After all, there are two sides to an issue.

In writing the history of the Horn of Africa before the colonial scramble, consulting the Chronicles of Ethiopian Emperors such as Amde Tsion [1312-1342], Dawit [1382-1411], Yeshaque [1414-1429], Zere Yacob [1434-1468], and Sertse Dingil [1563-1597] becomes crucial. What is worthy of note is that some of the chronicles are accessible even in foreign languages. For example, *The Glorious Victories of Amde Tsion* is available in German [Dillmann, 1884], in French [Perruchon, 1889], in Italian [Conti Rossini, 1900], and in English [Dr Huntingford, 1965]. Yet, let alone examine manuscripts in Geez, Amharic, Tigrigna or other Ethiopian languages, the supposedly "scholarly" works on Ethiopia have not even been provided depth and illumination from the translations. Although they appear in academic format, they are completely superfluous. It is evident that they have been produced to serve other purposes than to help advance knowledge and scholarship. " ይላል ዶ/ር ዳኒኤል "Was the Ogaden handed over to Ethiopia by Britain in 1896?" በሚል ታሪካዊ ጥናቱ።

ከዚህ ቀጥሎ የሚታዩት የዘመን መቁጠሪያዎች በሙሉ በአውሮጳ ዘመን አቆጣጠር ነው። ስተረጉመው በጣም ቀላል በሆነ አቀራረብ እና አጠር ባለ አንባባን እንደሚገባ አድርጌ ለመረጃ ያቀረብኩት ታሪካዊ የታሪክ የሰነድ መረጃ ነው።

እንግዲህ ደ/ር ዳኒኤል የሚለው በ1896 ነው ኦጋዴን ጉዳይ ወደ ክርክር የመጣው (በቅኝ ገዢዎች)። ዓረብ ነኝ የሚለው ኦብነግ ደግሞ በትንሽዋ ጭንቅላቱ በ1954 ነው ለኢትዮጵያ የተሰጠ ነው የሚለው። በ18ኛው ይሁን በ19ኛው የኦብነግ ጥያቄ ሕጋዊ አለመሆኑን ነው የምንነጋገረው። ዳኒኤል ክንዴ ከላይ የሚለው ባጭሩ ለመግለጽ "ሁሌም እንደሚደረገው (ስለ ኦጋዴንም ሆነ ስለ አገራችን ጉዳይ) ከውጭ በኩል የሚቀርቡ ሰነዶች/ምርምሮች እውነታውን ለማስረገጥ ከውስጥ

ሰነዶች እና ታሪኮች ጋር እያስተያዩ በጥንቃቄ መመርመር አለባቸው በማለት ነው የሚመክረን።

እዚህ ላይ በውጭ አገር ምሁራን የሚቀርቡ አንዳንድ ሰነዶች ግሩም ምርመራ ተደርጎባቸው የተሰነዱ አሳማኝ ሰነዶች  አሉ።በአንጻሩ ደግሞ፤ በስመ ምሁር ነኝ ባይነት የተጣመመ፤ የተሳሳተ ሰነድ በማቅረብ የተበላሸ ስራ የሚሰሩ ሰዎች አሉ። አስፈላጊው "ምሁርነት" ብቻ በቂ አያደርገውም። ስለ አካባቢው ጉዳይ ሲጠና ያገሬው ውስጥ ቋንቋ ከሚደረግበት ጥናት ጋር እያስተያዩ ከጥንት ሰዎች ለትውልድ ተሰንደው የተውልንን የታሪክ ሰነዶች ምን እንደሚሉ የያዙት ፍሬ ነገር እያስተያዩ መሰነድ/መመዝገብ ዋነኛው የብልቱ ማሳያ መብራት መሆን አለበት።

አገራዊ ሰነዶችን ያሰፈሩትን ዘገባዎች በጥናታቸው ላይ ሳያገናዝቡ ስለ ኦጋዴንም ሆነ ስለ ምስራቃዊ አፍሪካ አካባቢ የሚጻፍ ሰነድ፤ በተለይ እንደ እውነታ ተወስዶ የቅኝ ግዛት መዝገብ ቤቶች ያሰፈሩትን ሰነዶች እየጠቀሱ እንደ እርግጠኛ ታሪካዊ ሰነድ አድረገው ማቅረብ ጥናቱን ለማዘጋጀት ለሚከፍሏቸው "ፋይናነሰሮችን" ቀጣሪዎቻቸው ከመጥቀም አያልፍም። ለምሳሌ ኦጋዴንን እና አካባቢው በሚመለከት ስንመለከት

አመድጽዮን (1312-1342) ዳዊት፤  (1382-1411) ፤ ይስሐቅ (1414-1429) ፤ ዘርአ ያቆብ  (1434-1468)፤ ሰርፀ ድንግል (1563-1597) የመሳሰሉት አካባበውን ያስተዳዳሩት ነገሥታት የተውልንን ሰነዶች ለጉዳዩ ዓይነተኛ ምሰሶ ሰነዶች ናቸው። ኦጋዴን የማን ነው? የሚለውን መከራከሪያ ጭብጣችን ከነዚህ ነገሥታት ይጀምራል። በነዚህ ነገሥታት ዘመን ኦጋዴን ውስጥ የነበረች ሴት ከማን ጋር ተኝታ ማንን ለትውልድ በደም ተሳስራ እንደወለደችና ዛሬ ግን ኢትዮጵያዊያን "አይደለንም"እያሉ ያሉትን ደማቸው እና አጥንታቸው ከማን ጋር አንደተደበላለቀ የማያውቁ "ለማወቅም" የማይፈልጉ ችግር ያለባቸው ሰዎች ዛሬ እንሞግታቸዋለን።

ከላይ የጠቀስኳቸው ነገሥታት ኦጋዴንን አስተዳድረው ሲገዙ የነበሩ ደማቸው አጥንታቸው የከሰከሱበት የወላጆቻችን መሬት እና ድምበር ነው። ጉዳዩ ዋጋ የሚያስሰጠው እና ልብ ማለት ያለብን፤ በጣም ሩቅ ዘመን በተጠቀሱት ባስተዳደሩባቸው ዘመኖች በተጠቀሱት ነገሥታቶች የተሰነዱ አንዳንድ መረጃዎች በውጭ አገር ሰዎች በውጭ አገር ቋንቋዎች ተተርጉመው የሚገኙ ናቸው። ለምሳሌ፤ ይላል ደ'ር ዳኒኤል፤-

“ *The Glorious Victories of Amde Tsion* የሚለው በጀርመንኛ ቋንቋ (Dillmann, 1884)፤ በፈረንሳይ ቋንቋ (Perruchon, 1889]፤ በጣሊያን ቋንቋ (Conti Rossini, 1900)፤ እና በእንግሊዝኛ (Dr Huntingford, 1965) ተርጉሞዋቸው ይገኛሉ።

ሃቁ ይህ ሆኖ እያለ፤ እንኳን እና በትግርኛ እና በአማርኛ የተጻፉትን ሰነዶች መመርመር ቀርቶ “ስለ ኢትዮጵያ ጥናት ተመራማሪዎች” ናቸው ሚባሉ ሊቃውንት ከተተረጐሙት ሰነዶችም በቂ የሆነ ጥልቀት ያለው የፈነጠቀ ምርምር አላካሄዱም። ጥናታቸው የምሁር ምርምር ነው ተብለው ይቅረቡ እንጂ የኢትየጵያን ምንጮች ያላካተቱ፤ጥልቀት የጎደላቸው ሰነዶች ሆነው ለሴራቸው ማርኪያ የቀረቡ ምርምሮች እንጂ ለእውቀት እና ለምርምር የተዘጋጁ አይደሉም። .....በማለት ነው ባጭሩ ደ/ር ዳኒኤል በአካባቢው ጥናት አቅርበናል የሚሉ ከቅኝ ገዢዎች መዛግብት ማሕደር ቤት የሚያገኙትን እንደ ቁም ነገር እየጠቀሱ የሚያቀርቡትን ተመራማሪዎች ነን ባዮችን ዶ/ር ዳኒኤል ክንዴ በተጨባጭ እና በተገቢ ይተቻቸዋል።

ደ/ር ዳኒኤል ክንዴ በኦጋዴን ላይ ያቀረበው ኢትጵያዊያን ነገሥታት የተውትን ታሪካዊ ሰነዶችን ዘመኖችን እያጣቀሰ ያቀረበው በጥልቀት ለማንበብ የእንግሊዝኛው ሰነድ ከላይ የጠቀስኩትን ርዕስ ገብታቸወሁ ጉግል ብታደርጉ ዝርዝሩን በጥልቀት ታገኙታላችሁ። እስከዛው ግን በአማርኛ አንዳንዶቹን ለማስረጃ ለኦብነጎቹ እንዲማሩበት (ማንንቱን የካደ፤ ዓረብ ነኝ የሚል መማር አይፈልግም እንጂ) መረጃዎችን እጠቅሳለሁ።

ከዶክተር ዳኒኤል ክንዴ ጋር በእዚህ ጽሑፍ ላይ አያይዤ፤ ሳላመሰግናቸው የማላልፋቸው ኢትዮጵያዊው የሙቶ አለቃ አያል ሰው ደሴን ሳላመሰግን አላልፍም።ምክንያቱም እሳቸውም በሚገባ ስለ ኦጋዴን ጉዳይ አንስተው ካሁን በፊት ከጻረ ኢትዮጵያው ከኦብነግ ወዳጅ ከሆነው ከአምባሳደር ‘ዴቪድ ሼን’ ጋር የተከራከሩበትን አኩሪ ሰነድ በማቅረባቸው ምስጋና አደርስላቸዋለሁ።

ዶ/ር ዳኒኤል ክንዴ እንዲህ ይላል።

“In historical terms, today’s Djibouti and Somaliland were part of the Ethiopian State centered in Axum. For example, the well known port of Zeila was one

of Axum's major outlets to the sea along with Adulis and Swakin. Since the Ethiopians invaded the Hedjaz and occupied Jeddah in 702 A.D, the Arabs were able to take the Dahlaque Islands and Massawa in retaliation."

በታሪክ የዛሬዎቹ ጁቢቲ እና ሶማሊ-ላንድ ዋና ከተማው አክሱም ያደረገው የኢትዮጵያ መንግሥት ክፍለ ግዛቶች የነበሩ ናቸው። ዜላ የተባለው አሁን በሶማሌ ግዛት ውስጥ የሚገኘው ወደብ አዱሊስ እና ስዋኪን (ፓርት ሱዳን ውስጥ ያለው ማለቱ ነው) ከሚባሉት የባሕር ወደቦች አክሱም ከሚቆጣጠራቸው ዋነኞቹ የባሕር ወደቦች አንዱ የነበረ ነበር። ይላል ።

አክሱም መቀመጫው ያደረገው ኢትዮጵያዊ መንግሥት (አነ ሳይዛና (አብርሃ አጽብሃ) ከተማውን የረር አድርጐ የየካን ሚካል እና የመሳሰሉት የዋሻ ቤተ/ክርስትያኖችን መገንባታቸው እና ፤ምዕራብ እና ደቡብ ኢትዮጵያ አልፎም እስከ ኬኒያ...ማስተዳደራቸውን ሳትዘነጉ- በጣም ጥነት ፤ጥንት፤ጥንት ማለቴ ነው) ሆኖም የምፅዋን ወደብ ነጥቀውት የነበሩትን ዓረቦች ተመልሶ በ854 A.D ሲነጥቅ፤ ዜላ ወደብ በ977ም ኢትዮጵያዊአን ያስተዳደሩት የነበረ ነው።

እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን፤ የቆላማውና የደገኛው ግጭት በቀጣይነት የተደረገ ሳይሆን አለፍ አለፍ (intermittent) ብሎ ነው የተከሰተው። ይላል ደ/ር ዳኒኤል ክንዴ።

እሩቅ ሳንሄድ በቅርቡ አፄ አምደጽዮን ዜላን በ1328 አስፈላጊው የሆነ ጥገና እና ስምሪት እንዲሁም አስተዳዳር ሲያደርገለት የነበረ ኢት ጵያዊ ወደብ ነበር። በወቅቱ የአካባቢው እስላሞቹ መሪዎች የነበሩት እንደ እነ አዳል፤ዳዋሮ፤ኢፋት፤፤ ሃዲያ፤ ፈጠጋር የመሳሰሉት ቦታዎች በንጉሡ ሥር ሆነው ለንጉሡ ገባሪዎች ሆነው የቆዩ (tributary states ) ናቸው።

ቀጥሎም ንጉሥ ዳዊት (በነገራችን ላይ በቅርቡ አዲስ አበባ ውስጥ ቤተ መንግሥቱ የነበረው ሥር መሬት ውስጥ ተቀብሮ የነበረ ጽሑፎች አብረው ግድግዳዎቹ ግምቡ ላይ) ከጥቂት ወራት በፊት ቤተ መንጌውቱ የተገኘው ነው)። ንጉሥ ዳዊትም ከወላጁ ከአምደ ጽዮን የተረከበውን የግዛት አስተዳዳር በማጠናከር የመከላከያ ድምበሮችን፤ እራሱ እና ወላጁ የሾማቸው የአካባቢ መሪዎችን (አሚሮችን....) በማስተዳዳር ቀጠለበት።

ከዚያም ንጉሥ ይስሐቅ ከዳዊት ተረክቦቦ አስተዳደሩን በማስፋት የተረከበውንም የዜላ ባሕር ወደብን በሚገባ ውስጣዊ ተሓድሶ እና ጥገናዎች በማድረግ አጠናክሮ ወደቡ ዋነኛ በር አድርጎ ተገልግሎበታል። ወደቡ ከመካካለኛ ምስራቅ አካባቢ አገሮች ከዚያም እስከ ሩቅ ምስራቅ ድረስ ንግዳዊ ግንኙነት በማድርግ በተለይ በ14ኛ 15ኛ 16ኛው ክፍለ ዘመን ነገሥታቶቹ የጦፈ ንግድ ሲያስተዳድሩበት የነበረ በተፈጠረው ኢትዮጵያዊ የንግድ ልውውጥ የባሕር ወደብ ንግዱ የአጋዴኖችን ኑሮ ይጠቅም ነበር።

እፁብ ድንቅ የሚያሰኘው ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ "ሶማሊ" የሚል ቃል በንጉሥ ይስሐቅ ዘመን የተደረሰው ዜማ ውስጥ ለድሉ የተዘመረለት መዝሙር ውስጥ ተጽፎ ይገኛል።

ወዳጄ ዶ/ር ዳኒኤል ክንዴ በግሩም የታሪክ ስነዳው እንዲህ ይላል፤

በተከታታይ ያለፉት ኢትዮጵያዊያን ነገሥታት የጀመሩትን ግዛታዊ ቁጥጥር (1434-1468)፤ በዘርአ ያዕቆብ ተጠናቀቀ። አዳልን ፤መቃዲሾን፣ ብራቫ እና መርካ በኢትዮጵያ እና በኢስያ አገሮች የሚካሄዱ የንግድ ልውውጦች በሚገኙት ግብይቶች ኢትዮጵያ በምታወጣው መተዳዳሪያዎች እየተዳደሩ ኑሮአቸውን ይመሩ ነበር።

ዳኒኤል ይቀጥል እና

"Harar was built as a civilization by the Adere – an Ethiopian community, still there, and who speak a language that is very close to Amharic."

ሐረር በአደሬ ኢትዮጵያዊያን ማሕበረሰብ ሥልጣኔ የተገነባች ነች። አደሬዎች ለአማርኛ (እና ለትግርኛም) ቅርበት ያለው ቋንቋ የሚናገሩ ማሕበረሰቦች ናቸው።

Sertse Dingil (1563-1597) led an army of considerable strength and brought an end to Harar as a military power. On his way to the province of Enarya ( today's Illubabor and Keffa provinces) , the same emperor paid a working visit to Gojjam, Damot, what is now called Wollega, Limu,

Jimma, Hadya, Gurage, Kembata, and Bale. Sertse Dingil baptized the Enarya leader, Sebenhi, and his son Bedancho, and according to his chronicle, he gave the son the Christian name of Zemariam. Before returning to his capital, he reduced Enarya's payment of annual tax by 50%.

በ1577 አጼ ሰርፀ ድንግል፤ከዚያ አናርያ( ዛሬ ኢሊባቡር እና ከፋ ተብለው የሚታወቁት ጠ/ግዛቶች (ክ/ሐገሮች)፤ ከዚያ የግዛት አስተዳዳሩን እና የሥራ ጉብኙቱን በመቀጠል ጎጃምን፤ዳሞት፤ እና በዛሬው አጠራር ወለጋ ፤ሊሙ፤ ጅማ፤ ሀዲያ ፤ጉራጌ፤ ከምባታ እና ባሌን ጎበኙ። ሰርጸ ድንግል የእናርያው መሪ የነበረው "ሰበንሒ" ን (ክርስትና) አጠመቀው። ቀጥሎም ልጁን "በዳንቾ" ን አጥምቆ "ዘማርያም" ብሎ የክርስትና ስም እንደሰጠው በንጉሡ የዜና መዋዕል ተጽፎ ይገኛል። ንጉሡ ወደ መናገሻው ከመመለሱ በፊት የእናርያኖች የግብር ዕዳ ሲከፍሉት ከነበረውን ዕዳ ወደ ግማሽ (50%) ዝቅ አድርገው እንዲከፍሉ ትዕዛዝ አስተላልፎላቸው ሄደ።

"With this background, let us turn now to the modern period. The British established themselves in 1887 in what was to become British Somaliland- a country of 180,000 sq. kms with half a million inhabitants, in order to find a source of cheap food supplies for their garrison in Aden, where they had 182 officers. They also wanted to control the strategic Strait of Bab-el-Mandeb, and to keep an eye on the French, who had already established themselves in Djibouti in 1884. Furthermore, the British occupied the Sudan in the 1880s and Kenya in 1890. Largely encouraged by the British, who betrayed Ethiopia, and in a clear breach of the obligations set down in the Adwa Treaty of

1884, the Italians took over Massawa in 1885, and what became Italian Somaliland in the 1880s."

ይህ የታሪክ ንጣፍ/ጉዝጓዝ/መሰረት ይዘን ወደ ዘመናዊው ክ/ዘመን ትኩረታችንን እናዞር። እንግሊዞች በ1887 ሶማሊ ላንድ ተብሎ የሚጠራውን ግማሽ ሚሊዮን ሕዝብ ያቀፈ እና በ180,000 sq. kms ስፋት የሚገኘውን ሶማሊ ላንድ በወቅቱ አደን (የመን) ውስጥ 182 መኮንኖች/ወታደሮችን አሰማርቶ ለነበረው ወታደራዊ ሰፈራቸውን መመገብ እንዲችሉ ለርካሽ ጥሬ ዕቃ ፍለጋ ሲሉ ቦታውን ተቆጣጠሩት። በተጨማሪም በ1884 ጅቡቲን የተቆጣጠሯትን ፈረንሳዮችን ለመቀናቀን እንዲያመቻቸው ባብ ኤል ማንዴብ የተባለው ስርጥ የባሕር ቁልፍ መሬት ለመያዝ ፍላጎት ስለነበራቸው ሶማሊ ላንድን እንደ ማስፈንጠሪያም እንደ የርካሽ ዋጋ የሸቀጥ ገቢ መገልገያም ለማድረግ ያዟት። በተያያዥ፣ እንግሊዞች ሱዳንን በ1880 እና ኬኒያንም በ1890ዎቹ ተቆጣጠረ። በተጓዳኝ ባብዛኛው ማለት ይቻላል፣ በእንግሊዞች ድብቅ ገፋፊነትና መሰሪነት የ1884ቱን የዓድዋውን ውል በመጣስ ጣሊያኖች በ1885 ምፅዋን ያዙ።

በወቅቱ ነበሩት አፄ ምኒሊክ ናቸው። ንጉሡ በግራም በቀኝም በመሃልም ከታች እና ከላይ በጠላት የተከበበች ኢትዮጵያን ነው እያስተዳደሩት ያሉት። ንጉሡ በሁኔታው ሥጋት አደሮባቸዋል። ስለሆነም፣ የግዛታቸውን ዳር ድምበር ለማሳወቅ በ1981 አካባቢውን ለተቀራመቱት የቅኝ ግዛት ተስፋፊዎች በጻፉት ደብዳቤ ላይ "የሩቅ ሃይሎች መጥተው አገሬ አፍሪካን ለመቀራመት ሲመጡ እኔ ቆሜ ቅርምቱ ሲፈጸም በታዛቢነት የማልፍበት ትዕግሰት የለኝም"። በማለት የጻፉላቸውን ደብዳቤዎች እውን በማድረግ ዓድዋ ላይ ጣሊያኖችን ገጥመው በ1896 (1888 ዓ.ም) ድል አደረጓቸው። ሆኖም፣ እፍኝ የማይሞሉ ግራ የገባቸው "ምሁራን ተብዬዎች" የምሁራን ደናቁርት የንጉሡን አኩሪ አቋም እና ደብዳቤ "አፍሪካን ስትቀራመቱ እኔም አብሬአችሁ ልቀራመት" ብለው ነፃ አገሮችን ወርረው እሳቸውም የቅርምቱ ተካፋይ ሆነዋል፣ እያሉ በማይመስል ትርጉም እያጣመሙ ደብዳቤውን ተርጉመውታል።

ሆኖም እኛ የኢትዮጵያን ታሪክ ያጣናን የታሪክ ምሁራን ግንዛቤ፣ አንባቢዎች እንዲረዱት የምንፈልገው ቁም ነገር "ምኒሊክ" በታሪክ የኢትዮጵያን ግዛት ያልነበረ አንዲት ኢንች የምታክል መሬት አንኳ አልወሰዱም። ይህ ሁሉ የሴራ ጉንጉና ከጠላቶች የመጣ ነው። ሳይወሩት ለመውረር የመጡትን ወራሪ ጣሊያኖችን ለመቋቋም የኢትዮጵያዊያን እና መሪዎቹ ቆራጥ እና አርበኛዊ ውሳኔ ዓድዋ ላይ

የተገኘው ድል በቂ መረጃ መሆኑንና ገላጭ ነው። ይህ ሁሉ የታሪክ ውሸት፤ነገርን ማጣመም፤ማስፈራራት እና ተከታታይ የሆነ የኢትዮጵያን ታሪክ እንደገና ለመጻፍ እየተደረገ ያለው ሴራ የሚያመለክተው ኢትዮጵያ ያስመዘገበቺው አፍሪካዊ አርአያነት እና ጸረ ቅኝ ግዛት አቋም በጠላቶች እና በተቀጣሪዎቻቸው ልብ ውስጥ ፍራቻ እና ውርደት ስላሳደረበቻቸው መሆኑን ግልጽ ነው።

ይህንን አውነታ በሚመለከት እራሳቸው በእንግሊዞቹ ስፔክታቶር (March 7, 1896) በሚባል ጋዜጣቸው ወደው ሳይወዱ የሚከተለውን መስክረዋል፦

"The Italians have suffered a great disaster, greater than has ever occurred in modern times to white men in Africa. Adowa was the bloodiest of all colonial battles."

France described

"Ethiopia as a country which could pose political questions of great importance. "

A French journalist viewed it in a similar fashion when he said:

"All European countries will be obliged to make a place for this new brother who steps forth ready to play in the Dark Continent the role of Japan in the Far East."

ትርጉሙም ፡

"የዓድዋ ጦርነት የቅኝ ግዛት ጦርነቶች ተካሁደዋል ተብሎ ታሪክ ከዘገባቸው የቅኝ ግዛት ጦርነቶች ሁሉ ከፉ ውግያ ነበር። ጣሊያኖች በዚያው ጦርነት  እጅግ በጣም ኩፍኛ የውርደት ውርደት የሆነ ሽንፈት ተከናንበዋል። ይህ የሽንፈት ስቃይ በማንኛውም በዚህ የሥልጣኔ ዘመን ማንም የነጭ ዘር ሰው ተከናንቦት የማይታወቅ የጥቁር አፍሪካኖች ሃያልንት የታየበት የነጭ ሰው ውርደት እና ሀፍርት ዓድዋ ላይ ለመጀመሪያ ሊከሰት የመጀመሪያ ነው።"

ፈረንሳዮች እና ጋዜጠኞቻቻውም፤ እንዲህ ብለዋል፡-

ሁሉም የአውሮጳ አገሮች በቅርቡ የታየው አዲስ ጉዞ እና ሃያልነቱን ያስመሰከረው ፤ በጥቁሩ ክ/ዓለም ተገቢውን ሚና እንደ ብረቱዎቹ እንደ እሩቅ ምስራቆቹ እንደ ጃፓኖቹ ማንነቱን ለማሳየት የተነሳው ለአዲስ ወንድማችን ተገቢውን ክብር እና ቦታ እንስጠው" (ይህ ያሉበትም ምክንያት ጃፓኖች ቻይናን በ1895 እና ሩሲያን በ1905 ስላሸነፈች ነው ጃፓንን በምሳሌ ከኢትዮጵያ ጋር በማመሳሰል የጻፉት)

እንግዲህ የዛሬዎቹን የምኒሊክ እና የዓድዋን ድል የሚያጥላሉ ተገንጣዮች ለምን አንዲያ እንደሚሉ የተዋቀ ነው። ግንጠላቸውን ለማሳካት ሲሉ ኦጋዴን ፤ኦሮሚያ ምንተስ ምንትስ...... የተባሉ ነፃ የነበሩ አገሮች ነበሩ፤ ምንሊክ ወደ ኢትዮጵያ የቃለቀላቸው እንግሊዝ ለኢትዖጵያ (በ1954) ኦጋዴንን ለኢትዮጵያ የሰጣቻቸው መሬት ነው፤ እያሉ የሚቃዡት ከዚህ ግንጠላ ተልእኮ የተነሳ አባዜ ነው።

ጣሊያኖች በደረሰባቸው ሽንፈት ምክንያት ፤ አንግሊዞች ከጣሊያኖች ሽንፈት ወዲያ በጣሊያኖችን አካባቢ ቅርምት እና መረጃ እና አጋርንት(Italians as their watch-dog in Northeast Africa) መተማማን ስላልቻሉ እንግሊዞች በቀጥታ ወደው ሳይወዱ ከሃያልዋ ከኢትዮጵያ ጋር መነጋጋር ነበረባቸው። በዚህ መሰረት ሁሉም ጣሊያኖች፤ ፈረንሳዮች፤ እንግሊዞች የድምብር ከለላ ሲያደርጉ ከብልሁ እና ከነበረው አፍሪካዊ ጠንካራ መሪ ከንጉሱ ከምንሊክ ጋር ነበር።ስለዚህም ከአካባቢው እና ብቻኛ መሪው የድምበር ከለላ ተካሄደ።

በዚህ መሰረት ኢትዮጵያ እና ጣሊያን በ1897 የድምበር ከለላ ለማድረግ ተስማሙ። በሁለት ካርታዎች የተነደፈ ምልክት ተደረገ። ይህ እንዲህ እያለ ካርታዎቹ ጠፉ ተባለ። በዚህ ምክንያት ጭቅጭቅ ተነሳ። ጭቅጭቁ ለማሳረግ ሲባል በ1908 ሌላ ስምምነት ተካሄደ። ከተደረገው ስምምንት ውስጥ "Article IV" በተባለው አንቀጽ እንዲህ ይላል፤-

"That all of the Ogaden shall remain dependent on Abyssinia (Ethiopia).

"መላው የኦጋዴን አካባቢ በኢትዮጵያ ድምበር ውስጥ ይሆናል"

ስምምነቱን በመሬት ላይ ተግባራዊ ለማድረግ የጋራ የድምብር ኮሚሽን 1911 ከለላው በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ እያለ ጣሊያን ከቱርኮች ጋር በነበራት ጦርነት ምክንያት አሁን አጣዳፊ ጦርንት ስለተከሰተ አልተመቸኝም ለጊዜው ብላ መካለሉን “አቋረጠቺው”።

ተከትሎ ፋሺስት ሙሶሎኒ 1922 ወደ ሥልጣን ሲወጣ ሞሶሎኒ ለየት ያለ አዲስ የፖለቲካ አጀንዳ ይዞ መጣ። አዲሱ ዓላማው “አድዋ ላይ በጣሊያን ወላጆቹ የደረው ውርደት ለበቀል” ነበር።

አንደተለመደው እንዳለፉት ሁሉ በፈረንሳዮች እና በእንግሊዞች አይዞህ ባይነት በ1934, ኢትዮጵያን ለመውረር እንዲያመቸው ምልክት ያልተደረገበትን የአቅራቢያ ድምብር በመጣስ 60 ማይል ውስጥ ወደ ኢትዮጵያ ድምበር ገብታ የምትገኘው የኢትዮጵያ ከተማ የሆነቺው “ወልወል”ን ገብቶ በመያዝ አዲስ ጸብ ጫረ። በወልወል ውስጥ የነበሩት ኢትዮጵያዊያን ጸብ ጫሪ ጣለያንን በቆራጥንት ሲመክቱት ፤ ሙሶሎኒም በለመደው የውሸት ምላሱ “ኢትዮጵያ” ጦርነት ከፈተችብኝ አለ። የተጠቀሰቺው ከተማ ደግሞ በዓለም አቀፍ እውቅና የተሰጠው የኢትዮጵያ መሬት ነው። ወልወልን ለመከላከል ብዙ ኢትዮጵያዊያን ጀግኖች ደም ጠይቋል (1934- 1941)። ሶማሌ ቅጥረኞችም የጣሊያን አስካሪስ/ባንዳዎች ሆነው ኢትዮጵያን ወግተዋል።

ዶ/ር ዳኒኤል ይህንን አስመልክቶ እንዲህ ይላል፡

“The defence of Walwal was the price Ethiopia had to pay in blood [1934-1941]. Italy used 800,000 soldiers, 600 aircraft, 400 tanks, 30,000 transport vehicles, and the extensive use of mustard gas to bleed Ethiopia to death. Some 40,000 Somalis, including the late Somali President Siad Barre were also mobilized in the invasion of Ethiopia. “

In 1941, the entire Horn of Africa came under British Military Administration, except Ethiopia, which lent the Ogaden to the British so that as an ally they could use it as

a base for conducting military operations against Germany, Italy, and Japan. The Ogaden was returned back to Ethiopia in 1948-49. When people say the British handed over the Ogaden to Ethiopia, may be they are referring to this situation.

Let me now put in a summary form why, in my view, Ethiopia's borders with Somalia are internationally recognized and have been confirmed on ten different occasions from 1897 to 1988.

1. On July 28, 1897, when the Anglo-Ethiopian Boundary Treaty was affirmed by the British Parliament and duly ratified by Queen Victoria;
2. On June 16, 1908, when the Italian Parliament ratified the Italo- Ethiopian Boundary Treaty of 1897 and the Convention of 1908. Duly concluded, signed and ratified, it legally binds the signatory parties and their successors, either directly or by right of devolution;
3. In 1923 when the League of Nations registered these treaties (art.1, para.3 and art.18), by the very fact of Ethiopia's membership to the League of Nations;
4. In 1934, when the members of the League of Nations accepted the 1908 Convention as the legal basis for solving the Italo-Ethiopian boundary dispute, and when Ethiopia went to war with Fascist Italy (1934-1941) in the defence of its eastern province;
5. In 1945, when the United Nations registered these treaties;

6. In 1950, when the United Nations General Assembly approved the Trusteeship Agreement of 2 December 1950, affirming that Somalia's boundaries with Ethiopia shall be those fixed by international agreements. In so far as they are not delimited, they shall be delimited in accordance with a procedure approved by the General Assembly;
7. In July 1964, when the OAU Heads of State Summit in Cairo adopted the Resolution (AHG/Res.16 (I) on the inviolability of state frontiers;
8. In 1964, when the Non-Aligned Heads of State Summit in its meeting in Cairo also decided that existing frontiers should be maintained;
9. In 1981, when the OAU Heads of State Summit in Nairobi declared that "the Ogaden is an integral part of Ethiopia."
10. In 1988, when the late President Siad Barre of Somalia singed an agreement in Djibouti with President Mengistu Haile Mariam of Ethiopia renouncing Somalia's claim to the Ogaden.

Ethiopian Somalis who live in the Ogaden want self-determination. To that end, they invoke the December 14, 1960 United Nations General Assembly Declaration on Self-Determination, Res. 1514 (XV). Such a declaration, in the issuing of which Ethiopia was a party, was never meant to be used as a means of challenging the unity and territorial integrity of sovereign states, but to speed up the decolonization process in the African continent. For

Ethiopia, therefore, the right of self-determination cannot have preponderance over the principle of sovereignty. Ethiopia should emphasize that Ethiopian Somalis, who live in the Ogaden Province, enjoy the right to govern themselves, to establish their own regional constitution, to elect their own representatives to regional and federal assemblies, and to use their language as a medium of instruction in schools, and in that way, they exercise the right to self-determination. One could add, for example, that if Somalia's views on self-determination are to be taken seriously, it should be the first to recognize the Republic of Somaliland because the majority of the citizens of that country have already voted for independence. "

በማለት ሊቁ ዶ/ር ዳኒኤል ክንዴ ኦጋዴንን አስመልክቶ አስደናቂ እና የሚያስመሰግን ታሪካዊ ሰነዱን ከላይ ባጭሩ አንዳቀረብኩላችሁ ደምድሞታል። ለሰፊው ጥናታዊ ጽሑፉን ለማንበብ ጉጉል ውስጥ በመግባት የሚከተለውን Was the Ogaden handed over to Ethiopia by Britain in 1896? ብላችሁ ብትጽፉ መላውን ይዘት ማንበብ ትችላላችሁ። ስላነበባችሁኝ እጅግ አመሰግናለሁ፤ ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ) getachre@aol.com